“ የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል::“
ትንቢተ ዳንኤል :- ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 :

# ግንቦት ሰባት

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ውዲቷ ኢትዮጵያ የዥንጉርጉር ምድር
የያቆብ አደራ የቃል ኪዳን ሀገር ::
ነቢዩ መሀመድ ያረጋገጡላት
የሰላም የፍቅር የደጋጎች እናት ::
የልጆችሽ ትዕግሥት መስሎ የፈሪዎች
ሊሸጡሽ ተነሱ የእናት ጡት ነካሾች ::
የተዳፈነ እሳት የጠፋ መስሎአቸው
ተረማመዱበት በቀን ቅዥታቸው ::
ትዕግሥት ተሚጠጠ አለፈ ለከት
እንግዲህ ሊታይ ነው ኢትዮጵያዊነት
ብርሀኑ መቶ ጠፋ የግንቦት ነፃነት
ዳግም ተወለደ የስላሴዎች ዕለት ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

በባድሜ በአሰብ የሚነደው ውስጣችን
መቼ እንቅልፍ ተኛን ዝም ቢል አፋችን ::
ዝምታ መቀበል መስሎአቸው መለስ
ድጋሚ ተነሱ ድንበር ለመቁረስ ::
መይሳው ካሳ የተወለደበት
የዮሐንስ እራስ የተቆረጠበት ::
ከቶ እንዳያስቡ ቋራ መተማን
ደም የፈሰሰበት የአባቶቻችን ::
ለከት ያጣ ትዕቢት እንዲህ አይነት ድፍረት
መሆኑን ይወቁት መጨረሻው ውርደት ::
ሸሬ እንደስላሴ አንገቱን ቢደፋ
ዥንጉርጉሩ ነብር መቼ አንቀላፋ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ለሰላም ለፍቅር ለሕዝብ አንድነት
ቴዎድሮስ በዘፈነ ለኢትዮጵያዊነት ::
ሰበብ ተፈብርኮ ጨለማ ሲታጎር
አይደለም ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ነው ማሰር ::
ከመሪው ጀምሮ እስከ በታች ሹሞች
የሀገር ሀብት ሲዘርፉ እንደ ተራ ሌቦች ::
ሕዝብ ሊያስተዳድሩ ሥልጣን የጨበጡ
ብረት አሰርተው ወርቅ ሲለውጡ ::
እረ የእምዬ ልጅ ምንድነው ዝምታ
ምን እስኪፈጠር ነው የምታመነታ ::
ግንቦት ሰባት ያሉ ያስፈጠራቸው ጭንቅ
ተነሳ ይሉሀል ነገን አትጠብቅ ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ለመለስ በረከት ለስብሀት ህልም
አራት ሚሊዮን ጅብ ለሆዱ ቢያድርም ::
እንደ ሞኙ በሬ ውለው ከአራጃቸው
አይቀርም በቅርቡ ቅርጫ መሆናቸው ::
ይኸው ምልክቱ ታይቷል በመተማ
ማን ደረሰላቸው ንብረት ሀብት ሲቀማ ::
የሲቃ ድምፃቸው ሲደመጥ ከእስር ቤት
ውሸታም ተባሉ በመለስ ምክር ቤት ::
ነግ በኔን አትርሳ ለወያኔ ያደርክ
ጠንቅቀህ እውቀው ባለተራ እንደሆንክ ::
በጥቃቅን ጥቅም የታወረ አይንህ
ነገ እንዳያፍሩብህ አሰብ ለልጆችህ ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ከወያኔ ጋራ ኢንቨስትመንት ማለት
የአህያና የጅብ የቀን ወዳጅነት
በመራራው ስደት ለፍተው ለዘመናት
በውርደት በስቃይ ያፈሩት ንብረት ሀብት ::
በወያኔ ታምነው ቱልቱላው ማርኳቸው
በልማት የዋሉ በገዛ አገራቸው ::
ተቃጥሎ በሱዳን ንብረትና ሀብት
እንደ ወንጀለኛ ታጉረው እስር ቤት ::
በግላጭ ካዳቸው የጅብ ወዳጃቸው
በወያኔ ሚዲያ ስም አጥፊ አላቸው ::
ይህን ግፍ ሚሸከም የቱ ነው ሀበሻ
ሆዱን ሚያነፈንፍ እንደ መንደር ውሻ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ኦሮሞ ኦጋዴን የሲዳማ አርነት
መገንጠል ኤርትራን መች አየን ሲበጃት::
ለአቶ መለስ ውጥን እኛ ተመቻችተን
እርስ በእርስ ስንታሽ የማይሆን ህልም ይዘን ::
በገዛ ሀብታችን ይዘዋል ግንባታ
ጥለውን ሊሄዱ ቀን የከፋ ለታ::
ምንድነው ሚስጢሩ ሁሉ ወደ ትግራይ
ሲዳማ ቦረና በረሀብ ሲሰቃይ ::
ኦሮሞ ኦጋዴን ጥይት ሚዘንብበት
ቂም ለማያያዝ ነው እንዳንኖር በአንድነት ::
ወገኔ ይብቃን ሁሌ አትበለጥ
ለግንቦቱ ራዕይ እራስክን ለውጥ ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ግልፅ ነው መንገዱ የግንቦት ሰባት ትግል
ፍትህ ነፃነትን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚል ::
የኢትዮጵያ ብሔሮች እኩል ሚኖርባት
የጋራችን ምድር በኢትዮጵያ ማምጣት ::
ሁሉም ባመነበት ተቀናጅቶ ትግል
ይህ ነው አማራጩ ወያኔን ለመጣል ::
በእውነት የቆመ ቅን ልቦና ላለው
ለእኛ የሚበጀን አንድነታችን ነው ::
አባቶች እናቶች የሃይማኖት መሪዎች
ግፍ በቃን ያላችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ::
ሁሉንም ድርጅት አሁን ነው ማስገደድ
በግንቦቱ ራዕይ ውይይት ይጀመር ጥላቻ እንዲወገድ

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ሰው ከተወያየ በንፁህ ልቦና
ልቡን ለይቅርታ ካደረገ ቀና ::
ከሌለው አጀንዳ ለሕዝብ የደበቀው
በግልፅ መወያየት ምንድነው ሚያስፈራው?
የሀገር ሽማግሌ የኢትዮጵያ ምሁሮች
እስላም ክርስቲያኑ የእምነት አባቶች ::
ተኩሰን ባንገድል ቃታ ባንስብም
ዝም ማለታችን ከገዳይ አያንስም ::
ደማቸው ይጮሀል ሁሌ በአምላክ ፊት
ለፍትህ ነፃነት መስዋዕት የሆኑት ::
የውይይት ጥሪ ለሁሉም ይድረስ
ለመጪው ትውልዶች ሰላምን ለማውረስ ::

**ከሚንበለበለው ከእሳቱ እቶን**
**ዳንኤልን ያወጣ የብርሀኑ መስፍን ::**
**ዛሬም አስታወሰን ሊያወጣን አርነት**
**አንዳርጋቸው ብለን በፀለይነው ፀሎት**
**ቸኮል አለ ልቤ ናፈቀ ውጤት**
**በጭንቅ ተወለደ ዳግም ግንቦት ሰባት ::**

ከ የአፅብአሔ
በርን - ስዊትዘርላንድ
ግንቦት 27 / 05 / 2008